# ትፈራርሳለች በተባለች አገር የተመዘገቡ አንጸባራቂ ድሎች

## (ክፍል አንድ)

ሲኢድ መሐመድ

በ1983 ወርሃ ግንቦት በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ አዲስ ነገር ተከስተ፡፡ ክስተቱ ለዘመናት ነግሶ የነበረውን የአፈና ስርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከስር መሰረቱ የናደ ነበር፡፡ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም በአፍሪካ ተወዳዳሪ ያልነበረው ሰራዊት የገነባ ስርዓት ተገርስሶ በኢትዮጵያ ደማቅ ታሪክ ተጻፈ፡፡ ግንቦት 20 ቀን 1983 ፡፡

አፋኙ የደርግ ስርዓት ከስር መሰረቱ በተገረሰሰ ማግስት ስለኢትዮጵያ ያልተባለ ነገር አልነበረም፡፡ በአገሪቱ የጎጠኝነት ፖለቲካ ሰፈነ፤ አገሪቱ ለጎሳ ጦርነትና ግጭት ተጋለጠች፤ ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ የምትባል አገር አትኖርም፤ ትፈርሳለች፤ ህዝቧም ይበተናል፤ መቋጫ የሌለው የእርስ በርስ ግጭትና ጦርነት ውስጥ ይገባል፤ የሚሉ ትንቢቶች በሰፊው ተስተጋብተው ነበር፡፡

የግንቦት 20 ደማቅ ታሪክ እነሆ 21 ዓመታትን አስቆጠረ፡፡ የደማቅ ታሪካዊነቱ መገለጫዎችንም በሰፊው አፈራ፡፡ አገሪቱ ለማመን በሚያስቸግር ፍጥነት በርካታ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ድሎችን መጎናጸፍ ቻለች፡፡ ለመሆኑ እነዚህ ድሎች ምን ምንድን ናቸው? ለኢትዮጵያ ህዝብ ያስገኙለት ፋይዳስ ምንድን ነው? የሚሉትን ለመገንዘብ ከ1983 ዓ/ም በፊት የነበረውን ሁኔታ በንጽጽር መቃኘት የግድ ይላል፡፡

ከ1983 ዓ/ም በፊት በኢትዮጵያ የተለየ የፖለቲካ አመለካከትን ማራመድ ፈጽሞ አይታሰብም ነበር፡፡ የተለየ የፖለቲካ አመለካከትን ማራመድ ቀርቶ በነበረው የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ሆኖ በፍትሃዊነት ማሰብ እንኳን አስቸጋሪ ነበር፡፡

ያ ዘመን የዜጎች የፖለቲካ ስልጣን ባለቤትነት የታፈነበት ዘመን ነበር፡፡ ስልጣን ላይ የነበረው ወታደራዊ መንግስት በጠመንጃ አፈሙዝ በመታገዝ ነበር የስልጣን እድሜውን ሲያራዝም የኖረው፡፡

በአገራችን የሚገኙ ከ80 በላይ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በገዛ አገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የሚቆጠሩበትና የራሳቸውን ቋንቋና ባህል መጠቀም እንደ ሃጢያት የሚቆጠርበት ዘመን ነበር ቅድመ 1983፡፡ የህዝቡ የፖለቲካ ስልጣን የታፈነበት እኩልነትና ፍትህ የራቀበት ዘመን፡፡

ከዚህ አንጻር ከሁለት ዓሰርት ዓመታት በኋላ ያለው ለውጥ ምን ይመስላል? የሚለውን ማየት ተገቢነት አለው፡፡ በኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት እውን ሆኗል፡፡ የተለያየ የፖለቲካ እምነት ያላቸው በርካታ ፓርቲዎች ተፈጥረዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በአሁኑ ወቅት 76 የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ፡፡ የፖለቲከ ድርጅቶቹ በስራቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ አባላትን አፍርተዋል፡፡

ይህ ደግሞ ዜጎች የፈለጉትን አይነት የፖለቲካ ድርጅት አባል የመሆንና እንደየፍላጎታቸው መደራጀት የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠሩን ያሳያል፡፡ ከ21 ዓመታት በፊት አንድ አምባገነን ፓርቲ ይመራት የነበረች አገር ባለፉት ዓመታት በተደረገው የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ ይህንን ያህል ቁጥር ያላቸው ፓርቲዎች ማስተናገድ መቻል ምን ያህል ድንቅ ለውጥ በዚች አገር መምጣቱን ለመገንዘብ ያስችላል፡፡ ከደርግ ውድቀት ጀምሮ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት እውን በመሆኑ በአፈሙዝ ወደስልጣን የመምጣት ዘመንም አብሮ አክትሟል፡፡

መንግስት በህዝብ ፍላጎትና ምርጫ ብቻ ወደ ስልጣን የሚመጣበት ስርዓት ተፈጥሯል፡፡ ባለፉት 21 ዓመታት የታየውም ይኸው ነው፡፡ እስካሁን ድረስ አራት አገራዊ፣ በርካታ የአካባቢና የሚሚያ ምርጫዎች ተካሂደዋል፡፡

ሕገመንግስቱ ከጸደቀ ከ1986 ዓ/ም ማግስት በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ በሆነው የ1987 ዓ/ም ምርጫ 57 የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፈዋል፡፡ ያ ለመጀመሪያ ጊዜ መድብለ ፓርቲ የተሳተፉበት ፍትሃዊና ነጻ ምርጫ በኢትዮጵያ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የከፈተ ነበር፡፡ በህዝብ የተመረጠ መንግስት ለመጀመሪያ ጊዜ አገሪቱን ማስተዳደር የጀመረበት ወቅት ነበር፡፡

የአገሪቱ ሕገ መንግስት በጸደቀ ማግስት በ1987 ዓ.ም የተኬሄደው ምርጫ ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ነበር፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ምርጫ ለኢትዮጵያ ህዝብ የመጀመሪያው ሲሆን ይህም ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የዓለም ሕብረተሰብን ያስገረመ ታሪካዊ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ህዝብ የፖለቲካ ስልጣኑን ያረጋገጠበት፣ በህዝብ የተመረጠ መንግስት ለመጀመሪያ ጊዜ ስልጣን የያዘበት እና በአገሪቱ አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት ነበር፡፡ የ1987ቱ አገራዊ ምርጫ፡፡

ከአምስት ዓመታት በኋላ በአገሪቱ ሕገመንግስት መሰረት የኢትዮጵያ ህዝብ ለሌላ ምርጫ ተዘጋጀ፡፡ ይኸው በ1992 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ 49 የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለውድድር ቀርበዋል፡፡ ይሄኛው ምርጫም እንደ 1987ቱ ሁሉ ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ነበር፡፡ ከኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በሁለተኛው አገራዊ ምርጫ ላይ ህዝቡ በሕገመንግስቱ የተረጋገጠለትን የፖለቲካ ስልጣን በመጠቀም ይጠቅመኛል ያለውን የፖለቲካ ፓርቲ በአገሪቱ ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ መርጧል፡፡

1997 ዓ.ም ሌላው ታሪካዊ አገራዊ ምርጫ የተካሄደበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህ ዓመት በአገሪቱ ተመስርቶ ስር እየሰደደ የነበረውን የዴሞክራሲ ስርዓት ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለመናድ የተነሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተሳተፉበት ምርጫ ነበር፡፡

ሕገ መንግስቱን ሕገወጥ በሆነ መልክ በመናድ ስልጣን ለመቆናጠጥ ከፍተኛ ጥረት የተደረገበት ወቅት፣ 1997፡፡ በዚህ አገራዊ ምርጫ አንድ ብሄር በሌላው እንዲነሳ፣ አገሪቱ ውስጥ የነበረው ሰላም እንዲደፈርስ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከሰላምና ልማት ወጥተው መቋጫ በሌለው የእርስ በርስ ጦርነት እንዲዘፈቁ ለማድረግ በተወሰኑ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያልተሞከረ ነገር አልነበረም፡፡

ሕገ መንግስቱ ያስገኘላቸውን በፖለቲካ ድርጅት የመደራጀት የመምረጥና የመመረጥ መብት ተጠቅመው ሕገመንግስቱን ለማፈራረስ ያልተቆጠበ ጥረት ያደረጉበት ወቅት ነበር፡፡ አገሪቱን እንደገና ወደ ነበረችበት የቀድሞ ስርዓት ለመመለስ ጥረት የተደረገበት ዓመት ነበር፡፡ አገሪቱን ወደ ሁከት ለማስገባትና በግርግር ለመጠቀም የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያልፈነቀሉት ድንጋይ ያልበጠሱት ቅጠል ባይኖርም የኢትዮጵያ መንግስት በወሰደው የሰከነ አመራር አገሪቱ የተረጋጋችና ሆና እንትትቀጥል አስችሏል፡፡ ህዝቡን የፖለቲካ ስልጣኑን ማንም በእብሪት ሳይነጥቀው ያስተዳድረኛል ያለውን የፖለቲካ ድርጅት መምረጥ ችሏል፡፡

በአንድ በኩል በምርጫ ተወዳድሮ ለማሸነፍ ይንቀሳቀሱ የነበሩት እነዚህ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምርጫው ባይሳካ በአመጽ ወደስልጣን ለመምጣት አልመው ሲሰሩ ነበር፡፡ ከምርጫ ማግስት ምርጫው ተጭበረበረ በሚል ሰበብ በአገሪቱ የማያባራ ግጭትና ብጥብጥ በመፍጠር በዚሁ መካከል ለመጠቀም ስትራቴጂ ነድፈው ይሰሩ ስለነበር ችግሩ ባቀዱት ልክ ባይሆንም እንዲፈጠር አድርገዋል፡፡ በዚሁ 36 የፖለቲካ ድርጅቶች የተሳተፉበት አገራዊ ምርጫ የህዝቡን የፖለቲካ ስልጣን ለመንጠቅ የተደረገው ጥረትም በበሳል አመራር ከሽፏል፡፡

በ2002 ዓ/ም የተካሄደው አራተኛው አገራዊ ምርጫ ከሶስተኛው አገራዊ ምርጫ የሚለይበት መሰረታዊ ነገር ነበረው፡፡ በሶስተኛው አገራዊ ምርጫ ከ130 በላይ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አባላት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የገቡበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ በአራተኛው አገራዊ ምርጫ የተሳተፉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር 63 ቢሆንም መመረጥ የቻለው አንድ አባል ብቻ ነበር፡፡

የፖለቲካ ስልጣን የህዝቡ በመሆኑ ህዝቡ የመረጠው የፖለቲካ ድርጅት አገሪቱን በማስተዳደር ላይ ይገኛል፡፡ ይህ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ለአገራችን ትልቅ ድል ነው፡፡ በኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መራር ትግል የተገኘው የግንቦት 20 ድል ለዘመናት ሲነሳ የኖረውን የህዝቦች የማንነት ጥያቄ የመለሰ ነው። በአገራችን የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት ተረጋግጧል፡፡ ሁሉም ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ወኪሎቻቸውን ያለምንም ተፅእኖ በነጻነት የሚመረጡበትና ሁሉም እንደ ብዛታቸው መጠን በእኩል የሚወከሉበት ስርአት ተፈጥሯል፡፡

ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን ማስተዳደር ጀምረዋል፡፡ በነጻነት መሪዎቻቸውን መርጠው የመተዳደር መብታቸው ተረጋግጧል፡፡ የአካባቢያቸውን ልማት በማፋጠን የልማቱ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋቸውን መጠቀምና ማሳደግ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በራሳቸው ቋንቋ ይጠቀማሉ፣ ልጆቻቸውም በመጀመሪያ ቋንቋቸው ይማራሉ፡፡ ሙሁራንና

ደራሲያንም በቋንቋቸው ይጽፋሉ፡፡ ወግና ባህላቸውን ያስተዋውቃሉ ያሳድጋሉ፡፡ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶቻቸውን በመጠበቅ ለዓለም ሕብረተሰብ በማስተዋወቅ ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ ለማግኘት የተቻላቸውን ጥረት ያደርጋሉ፡፡

በአገራችን የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸውን ቅርሶች በማስተዋወቅና በተባበሩት መንግስታት በቅርስነት እንዲመዘገብ ለማድረግ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የኮንሶ ብሄረሰብን በአብነት ማንሳይ ይቻላል፡፡ ይህ ብሄረሰብ እንደሌሎች የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሁሉ የተረሳ ነበር፡፡ ባህሉንና ቋንቋውን መጠቀም የሚችልበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ግን ቋንቋውንና ባህሉን ለማሳደግ እየሰራ ይገኛል፡፡

ለዚህ ማሳያ በ2003 ዓ.ም በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡትን በኮንሶ ባህላዊ መልክአ ምድር ላይ ያሉ ቅርሶችን መውሰድ ይቻላል፡፡ የኮንሶ ህዝብ ተራሮቻቸውን ለማልማት የሰሩት የእርሻ ላይ እርከንና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ለሁሉም የአገሪቱ አርሶ አደሮች መልካም ተምሳሌት የሚሆን ነው፡፡

የእነዚህ መካነ ቅርሶች በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት መመዝገብ የኮንሶና አካባቢው የቱሪስት መዳረሻነት ከማጠናከሩም በላይ ለአርሶ አደሩ ታታሪነትና ጥንካሬ እውቅና የሚያስገኝ ነው፡፡ የኮንሶ ህዝብ ለቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ያላቸውን ጥንካሬና ለባህላቸው እድገት ከሚያደርጉት ትግል ሌላው እንዲማርም ያግዛል፡፡ የኮንሶ ብሄረሰብ የማንነት መገለጫ የሆኑ የተለያዩ ባህላዊና ታሪካዊ እሴቶች ሳይበረዙ ተጠብቀው ከትውልድ ትውልድ እንዲሸጋገሩ ያግዛል፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸውን ቋንቋ፣ ባህልና ማንነት አክብረውና በራሳቸው ማንነት ኮርተው በኢትዮጵያውነታቸው የሚኮሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በመከባበር፣ በመተጋገዝና በእኩልነት መርህ ላይ ተመስርተው አዲስቷን ኢትዮጵያ ገንብተዋል፡፡ የአገራቸውን ህዳሴ እውን ለማድረግም ፈርጀ ብዙ ተግባራትን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ይህ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት ባለፉት ሁለት አሰርት ዓመታት የተገኘ ሌላው የግንቦት 20 አኩሪ ቱሩፋት ነው፡፡

ቅድመ 1983 ኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት ያልነበራት አገር ነበረች፡፡ ነጻ ፕሬስ ብሎ የሚታወቅ ነገርም አልነበረም፡፡ ቃሉም በአገራችን አይታወቅም ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ የግል ሚዲያ ሆነ የሃሳብ ነጻነት የሚባል ነገር አልነበረም፡፡

አንዳንድ በአውሮፓና በአሜሪካ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን የግል ሚዲያ አስፈላጊነት በተለያዩ ኢትዮጵያ ላይ ትኩረት ሰጥተው ይዘግቡ በነበሩ የውጭ ሚዲያዎች አልፎ አልፎ ሃሳባቸውን ያቀርቡ እንደነበር ቢታወቅም አገር ውስጥ በወቅቱ በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ምክንያት የፕሬስ ነጻነት ጭራሽ የሚታሰብ አልነበረም፡፡

በአገሪቱ የነበሩ ብቸኛ ሚዲያዎች ጥቂት በጣት የሚቆጠሩ ከመሆናቸውም በላይ የስርዓቱ ጉዳይ አስፈጻሚ ነበሩ፡፡ ሚዲያዎቹ የህዝብን አስተያየትና ፍላጎት የሚዘግቡበት በር ፈጽሞ የተዘጋ ነበር፡፡

ባለፉት ሁለት ዓሰርት ዓመታት የታየው ለውጥ ግን በእጅጉ ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ቅድመ 1983 ከነበረው ጋርም ጨርሶ ለንጽጽር ሊቀርብ የሚችል አይደለም፡፡

ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ኤጀንሲ የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በአሁኑ ወቅት በአገራችን 224 የህትመት 29 የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ተፈጥረዋል፡፡ ይህ ትልቅ እመርታ ነው፡፡ በርካታ የግል ሚዲያዎች በነጻነት የመንግስትን አሰራር ይተቻሉ፡፡ የየራሳቸው የኢዲቶሪያ ፖሊሲ በሚፈቅደው መሰረት በነጻነት ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ማንኛውም ዓይነት ዘገባ ይዘግባሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቅድመ ኢህአዴግ የመጽሃፍት ህትመት በዋዛ የሚታሰብ አልነበረም፡፡ አንድ ህትመት ቅድመ ምርመራን ማለፍ ይጠበቅበታል፡፡ ፍትሃዊነት በጎደለው ቅድመ ምርመራ ምክንያት ህልማቸው የከሸፈና ሞራላቸው የላሸቀ ደራሲያን ቁጥር የትየለሌለ ነበር፡፡

ይህ ነገር አሁን ላይ ቆመን ስናየው የተለየ ገጽታ ይዞ እናገኘዋለን፡፡ ማንኛውም ደራሲ ያለምንም ቅድመ ምርመራ ስራዎቹን ማሳተምና ማሰራጨት የሚችልበት ስርዓት ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በርካታ የግል ማተሚያ ቤቶች ተቋቁመዋል፡፡ ይህ ለበርካታ ደራሲያንና ምሁራን ትልቅ ፍስሃ ነው፡፡ ሃሳባቸውንና እውቀታቸውን ለህዝብ የሚያደርሱበት ሰፊ በር ተከፍቷል፡፡

ለበርካታ የአፍሪካ አገራት የልማት መጓተትና የድህነት መንሰራፋት ምክንያቶች ከሆኑት መካከል የሰላም እጦት በዋናነት ይወሰዳል፡፡ አፍሪካውያን ግጭት ውስጥ በመዘፈቃቸው ለርሃብ፣ ለስደትና ለእልቂት ሲዳረጉ ዘመናት አልፈዋል፡፡

ባለፉት ስርዓታት በአገራችን የነበረው ሁኔታም ከዚህ የተለየ አልነበረም፡፡ ደርግ ይከተለው በነበረው ጦረኛ ፖሊሲ ምክንያት በኢትዮጵያ ሰላም ርቆ ነበር፡፡ ከጎረቤት አገራት ጋር የነበረን ግንኙነት የሻከረ፣ የጀብደኝነትና የጦረኝነት ነጋሪት የሚደለቅበት ሁኔታ ነበር፡፡ አገሪቱ ቀዳሚነት ሰጥታ ታራምድ የነበረው ልማት ሳይሆን ጦርነት ነበር፡፡ ለልማት የሚመደበው ገንዘብም በእጅጉ ትንሽ ሲሆን የሚበዛው ገንዘብ በአፍሪካ በግዙፍነቱ ቀዳሚ የሆነ ሰራዊት ለመገንባት ይውል እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያሳያሉ፡፡ አገሪቱ የውስጥ ሰላምና መረጋጋት ከማጣቷም በላይ ከጎረቤት አገሮች ጋር የነበራት ዲፕሎማሲ የሻከረ፣ በእንካስላንቲያና በጦርነት መዝሙር የታጀበ ነበር፡፡

በአገሪቱ ሰፍኖ በነበረው የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብት አፈና ምክንያት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ከዓለም ሕብረተሰብ የተገለሉበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ኢትዮጵያውያን በግጭትና በጦርነት ተዘፍቀው፤ሰላም ጠምቷቸው፤ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ተደራርበውባቸው ለርሃብና ለእርዛት ተዳርገው ነበር፤ ቅድመ 1983 ፡፡

በዚህ ሁሉ የተወሳሰበ ሂደት ያለፉት ኢትዮጵያውያን ባለፉት 21 ዓመታት በነበረው ጉዞ ባደረጉት የተባበረ ጥረት ከሰላም ጋር ተያይዞ የነበረው ችግር መቅረፍ ችለዋል፡፡ የሰላም ዋጋ ምን ያህል ውድ እንደሆነ መንግስትና ህዝብ ተገንዝበዋል፡፡

በአገሪቱ የተንሰራፋውን ድህነት በማጥፋት  ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ የሚቻለው ውስጣዊና ከባቢያዊ ሰላም ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑ የተገነዘበው የኢትዮጵያ መንግስት ሰላምን ለማስፈን ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

ሰላምን ከማረጋገጥ አንጻር አንደኛ የውስጥ ሰላምን በሚገባ ማረጋገጥ  ሌላው ደግሞ በቀጠናውና በሌሎች የአፈሪካ አገራት ሰላምን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት የጎላ አስተዋጽኦ ማድረግ አገሪቱ የሚትከውናቸው ሁለት ተግባራት ናቸው፡፡

ከጎረቤት አገራት ጋር በሰላምና በሁለትዮሽ ጥቅም ላይ የተመሰረተ መደጋገፍና ትብብር በማድረግ ሰላማዊ ግንኙነት  የመፍጠር  አቅጣጫ መከተል የሚል ነው፡፡  ከዚህ በተጨማሪም በቀጠናውም ሆነ በአህጉሪቱ የሚፈጠሩ ግጭቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽእኖ ማሳደራቸው ስለማይቀር ሰላም እንዲሰፍን ማገዝ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ  ረጅም ርቀት መጓዟን ከኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያሳያል፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት መፈጠሩ ብቻ ሳይሆን በመላ አፍሪካ ሰላምን እውን ለማድረግ ኢትዮጵያ የላቀ ሚና ያላት አገር ሆናለች፡፡ በአፍሪካ የሰላም ማስከበር ሂደትም የላቀ ስፍራ  ይዛለች፡፡ አገሪቱ ሰላምን ለማረጋገጥ  እያደረገች ያለው ጥረትና እያገኘች ያለው ውጤት በተባበሩት መንግስታት ድርጅትና በአፍሪካ ህብረት ከፍተኛ ተቀባይነት እንዲኖራት አድርጓታል፡፡ በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ የነበራት ገጽታም ባለፉት ሁለት ዓሰርት ዓመታት ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል፡፡

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በአህጉሪቱ ሰላምን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ትርጉም ባለው መንገድ ለማገዝ 6 ሺ 400  ሰላም አስከባሪ ሃይል በሱዳን ዳርፉርና አብዬ፣ በላይቤሪያና በኮትዲቫር አሰማርታለች፡፡ ድህረ 1983 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግስት በአፍሪካ የሰላም ሂደት ድርሻውን ለመወጣት የሚያስችል የጠራ አቋምና አመለካከት  በመያዝ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1986 ዓ.ም የሰላም አስከባሪ ሃይል በሩዋንዳ ማሰማራቱ ይታወቃል፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰላም አስከባሪ ሃይል በተለያዩ የአፍሪካ አገራት ማሰማራቱን ቀጥሎበታል፡፡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ባለፉት 21 ዓመታት ከ35 ሺ በላይ የሰላም አስከባሪ ሃይል በተለያዩ ግጭትና ውጥረት በነገሰባቸው የአፍሪካ አገራት አሰማርቷል፡፡  በተለያዩ አገራት የተሰማራው የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሃይል በወታደራዊ ዲስፒሊን ታንጾ የተሰጠውን ሃላፊነት በሚያኮራ መንገድ እየፈጸመ መመለሱንና አሁን በተመሳሳይ መልክ እየፈጸመ እንዳለ መረጃው ይጠቁማል፡፡

ከዚህም አልፎ ኢትዮጵያ ጎረቤት ሶማሊያ በአሸባሪዎች እጅ በወደቀችበትና ህዝቧም ለስቃይ በተዳረገበት ወቅት ሰራዊቷን በመላክ የአልሸባብን አከርካሪ በመስበር ለሶማሊያውያንም ሆነ ለቀጠናው ሰላም እነዲሰፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገች ይታወቃል፡፡ አሁንም በተመሳሳይ መልኩ የሶማሊያን ህዝብ እያገዘች ትገኛለች፡፡

ትበተናለች! ትፈርሳለች! ህዝቦቿም መቋጫ የሌለው የእርስ በርስ ግጭትና እልቂት ውስጥ ይገባሉ በሚል የበግ ለምድ በለበሱ ነቢያት የተተነበየው ትንቢት መሰረት የለሽ ነበርና ደብዛው ጠፍቷል፡፡

ኢትዮጵያ አልፈራረሰችም፡፡ ህዝቧም አልተበተነም፡፡ ሰላሟም አልደፈረሰም፡፡ ያለፉት 21 ዓመታት የሚመሰክሩት ነገር ቢኖር ሀሳዊ መሲሓን እንደናገሩት ሳይሆን ኢትዮጵያ በአፍሪካ የሰላም አውራ መሆኗን ነው፡፡ አገሪቱ የራሷን ሰላም ከማረጋገጥ አልፋ ለአፍሪካ የሰላም አምባሳደር ሆናለች፡፡

ከላይ የቀረበውን ለማጠቃለል ያህል የህዝቡ የፖለቲካ ስልጣን መጎናጸፍ፣ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት መረጋገጥ፣ የፕሬስ ነጻነት እውን መሆን፣ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት መዘርጋት፣ የህዝቦች ዴሞክራሲያዊ መብት መረጋገጥና ሰብአዊ መብት መከበር አንድ ላይ ተደምረው ሲታዩ ኢትዮጵያ ባለፉት 21 ዓመታት በፖለቲካው ዘርፍ ቀላል የማይባል ጉዞ ተጉዛለች፡፡ ይህ የሚያሳየው አገሪቱ በርካታ ፖለቲካዊ ድሎችን መጎናጸፏን ነው፡፡  ትፈራርሳለች ተብላ የነበረችው ኢትዮጵያ እነዚህን ሁሉ ድሎች  አስመዝግባ ስናይ እውነትም የግንቦት 20 ድል አንጸባራቂ ፍሬዎችን ማፍራቱን  ለመረዳት አያዳግትም፡፡